# የመድኃኒት ጠቀሜታ ምንድን ነው?

የምግብና የመድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011“መድኃኒት”ማለት የሰውን በሽታ፣ የተዛባ ወይም ጤነኛ ያልሆነ አካላዊ ወይም አዕምሮአዊ ሁኔታ ወይም ተያያዥ ምልክቶችን ለመመርመር፣ ለማከም፣ ለማስታገስ ወይም ለመከላከል፤ የሰውን አካላዊ ወይም አዕምሮአዊ አሰራር በጠቃሚ መልኩ ለማስተካከል፣ ወደ ነበረበት ለመመለስ ወይም ለማሻሻል ወይም ከምግብ በስተቀር የሰውነትን መዋቅር ወይም ማንኛውንም የሰውነትን ተፈጥሮአዊ ተግባር በጠቃሚ መልኩ ለመለወጥ የሚውል ማንኛውም ንጥረ-ነገር ወይም የንጥረ-ነገሮች ውህድ ሆኖ ለእነዚህ ምርቶች ጥሬ ዕቃነት የሚውል ማንኛውንም ንጥረ-ነገር እንደሚያጠቃልል ያስቀምጣል።

መድኃኒቶች ከአራት የተለያዩ ምንጮች ከሆኑት ከእጽዋት፣ከእንስሳት፣ከማእድናትና በሰው ሰራሽ መልክ እንደመገኘታቸው በአሁኑ ሰዓት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የመድኃኒት አይነቶች ሳይንሳዊ መንገድን በመከተል ለተለያዩ የህክምና አገልግሎቶች በፈሳሽ፣ በእንክብል፣ በመርፌ ወዘተ መልክ ተዘጋጅተው ጥቅም ላይ እየዋሉ ይገኛሉ። እነዚህ መድኃኒቶች ከየትኛውም ጊዜ በተሻለ በሰው ልጅ ላይ የሚከሰተውን የጤና ችግርና ሞት በከፍተኛ ቁጥር ቀንሰዋል። በመቀነስ ላይም ይገኛሉ።

መድኃኒቶች እንደ አሁኑ ቁጥራቸው አድጎና በዘመናዊ መንገድ ተዘጋጅተው ለአገልግሎት መቅረብ ከመጀመራቸው በፊት የሰው ልጅ የተለያዩ የእፅዋት ክፍሎችን ለመድኃኒትነት ይጠቀምባቸው ነበር። ይህም የሰው ልጅ በየጊዜው የሚያጋጥሙትን የጤና ችግሮች ለመቅረፍ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ የህክምና ዘዴዎችን ሲጠቀም መቆየቱን ያሳየናል።

ከተፈጥሮ ምንጮች የሚገኙት (ከእጽዋት፣ከእንስሳትና ከማእድናት) መድኃኒትነት ያለውን ንጥረ-ነገር ከሌሎች አላስፈላጊ ንጥረ ነገሮች ለይቶ በማውጣት በርካታ ሂደቶችን በማለፍ ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው። በሰው ሰራሽ መንገድ የሚሰሩትም በሙከራ ላቦራቶሪ ምርምር ተደርጎባቸው ከበርካታ ሂደቶች በኋላ ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው።

መድኃኒቶች ከሚሰጡት ጠቀሜታ መካከል በሽታን መከላከል ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ነው። ለምሳሌ ክትባቶች ለእዚህ ጥቅም በማዋል ኩፍኝ፣የልጅነት ልምሻ፣የሳንባ ምች፣ማጅራት ገትር፣ ትክትክና የመሳሰሉትን በሽታዎች ከመከሰታቸው በፊት ክትባትን በአግባቡ በመውሰድ የሰውነት መከላከያ አቅምን በማዳበር እነዚህ በሽታዎች እንዳይከሰቱ ማድረግ ይቻላል።

ሌላው መድኃኒቶች በሽታን ሙሉ በሙሉ ለመፈወስ ይረዳሉ። ለምሳሌ የፀረ-ተህዋሲያን መድኃኒቶች በተዋህሲያን የሚመጡ በሽታዎችን ሙሉ በሙሉ ለመፈወስ ያግዛሉ። ከእዚህ በተጨማሪ በሽታን ለማከም ወይም በሽታው እንዳይባባስ ለመቆጣጠር ያገለግላሉ። አንዳንድ በሽታዎች ዘመኑ ባፈራቸው መድኃኒቶች ሊድኑ ወይም ሊፈውሱ የማይችሉ ናቸው።

ይሁንና ለእነዚህ በሽታዎች መድኃኒት ባለበት ወቅት ባይኖርም በሽታዎች እንዳይባባሱና የከፋ ጉዳት እንዳያመጡ ለመቆጣጠር የሚስችሉ መድኃኒቶች ግን አሉ።ለምሳሌ፡- ፀረ- ኤች አይቪ መድኃኒቶች የኤች አይቪ ቫይረስ መራባትን በመቀነስና በሽታን የመከላከል አቅም በማጠናከር በተጓዳኝ በሽታዎች እንዳይጠቁ በማድረግ የታካሚውን ጤናማ ኑሮን እንዲመራ ያግዛሉ።

መድኃኒቶች ከሚሰጡት ጠቀሜታዎች ውስጥ ሌላው የህመም ስሜታን ማስታገስ ነው። ለምሳሌ እንደ ፓራሲታሞል ያሉ መድኃኒቶች ለራስ ምታት፣ ለመገጣጠሚያ ህመም፣ ለትኩሳት ወዘተ ይታዘዛሉ። ይሑንና እነዚህ መድኃኒቶች በበሽታ ምክንያት የሚከሰቱ የህመም ስሜቶችን ከማስታገስ ውጪ በሽታውን ሙሉ በሙሉ መፈወስ አይችሉም።

አንዳንድ መድኃኒቶች ለተለያዩ የህክምና አይነቶች አንድ በሽታ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥም ያገለግላሉ። በአሁን ወቅት መድኃኒቶች አንድ ግለሰብ በህይወቱ በበሽታ እየተሰቃየ የሚቆይበትን ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ በመቀነስ ብቁና አምራች ዜጋ እንዲሆን ከማድረጋቸውም በተጨማሪ የሞትን ቁጥር በመቀነስ ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። እያበረከቱም ይገኛሉ። በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በሽታ ቀድሞ ከመከሰቱ በፊት በመከላከል ከተከሰተም የበለጠ ጉዳት እንዳያደርስ ለመቆጣጠርና ለመከላከል መድኃኒቶች ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው።

ሌላው መድኃኒቶች የቤተሰብ ቁጥርን በመወሰን ረገድ የሚደርጉት አስተዋፆኦ ከፍተኛ መሆኑ ይነገርላቸዋል። የተለያዩ የእርግዝና መከላከያ መድኃኒቶችን በመጠቀም ጤናማና የተመጣጠነ ቤተሰብን ማፍራት ይቻላል። በተጨማሪም በአስገድዶ መድፈር እና ባልተፈለገ የግብረ ስጋ ግንኙነት እርግዝና እንዳይከሰት ይረዳሉ።

መድኃኒቶች የሰውን ልጅ የጤና ችግር በመቀነስ የግለሰብን ብሎም የኅብረተሰብን ምርታማነት ያሳድጋሉ። ጤናው የተጠበቀ ዜጋ ያለውን ጊዜና ጉልበት ተጠቅሞ በመሥራት የራሱን የቤተሰቡን ብሎም የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ የራሱን አስተዋፆኦ ያደርጋል።

መድኃኒቶች ወጪን በመቀነስ ረገድም አንድ ግለሰብ በተለያዩ ጊዜያት በሚከሰቱ በሽታዎች የተባባሰ ደረጃ ላይ ደርሶ ላልተፈለገ ከባድ ወጪ እንዳይዳረግ የራሳቸውን ድርሻ አላቸው። የእንስሳትን ጤንነት ከመጠበቅ አንፃርም ቢሆን መድኃኒቶች በሽታን በመከላከል፣በማዳን እንዲሁም የበለጠ እንዲመገቡ በማድረግ በአርሶ አደሩ የምርት ሂደት ውስጥ ወሳኝ ሚና አላቸው። በአጠቃላይ መድኃኒቶች በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ወሳኝና የማይተካ ሚና አላቸው። ለመድኃኒቶች የሚወጣውም ወጪ ለጤና አገልግሎት ከሚወጣው አጠቃላይ ወጪ አንጻር ሲታይ ከፍተኛ ነው።

የመድኃኒቶችን አሰያየም ስንመለከት አንድ መድኃኒት እስከ ሶስት የሚደርሱ ስሞች ሊኖሩት ይችላሉ። እነዚህም ኬሚካላዊ ስም(Chemical Name)፣ የፅንስ ስም (Generic Name) እና የንግድ ስም (Brand or Trade name) ናቸው።

ኬሚካላዊ ስም የመድኃኒቱን መሰረታዊ የተፈጥሮ ይዘት መሰረት በማድረግ የሚሰጥ ስም ሲሆን ማንኛውም መድኃኒት የራሱ ኬሚካላዊ ስም ይኖረዋል። ብዙዎቹ መድኃኒቶች ረዘም ያለ ኬሚካላዊ ስም ስለሚኖራቸው ይህ ስም ከህክምና ጋር በተያያዘ በብዛት ጥቅም ላይ አይውልም።

ሌላው የጽንስ ስም ነው። ይህ ስም ከኬሚካላዊ ስም በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ዙሪያ ሊያግባባ የሚችል ለአንድ መድኃኒት የሚሰጥ ስም ነው። ይህም አንድን መድኃኒት ለመገበያየት፣ለማዘዝ፣ለማደል ወዘተ ከኬሚካላዊ ስም ይልቅ አጠር ያለ በመሆኑ በስፋት የምንጠቀምበት ስም ነው።

ከላይ ከተጠቀሱት የመድኃኒት ስሞች በተጨማሪ አንድ የራሱ የሆነ ኬሚካላዊና የጽንስ ስም ያለው መድኃኒት ባመረተው ድርጅት ሶስተኛ ስም ሊሰጠው ይችላል። ይህ ስም የንግድ ስም የሚባል ሲሆን የአምራች ድርጅቱን ምርት ከሌላ ድርጅት ምርት ለመለየት ታስቦ የሚሰጥ ስም ነው። በመሆኑም አንድ መድኃኒት በርካታ የንግድ ስሞች ሊኖሩት ይችላሉ። በእዚህም ምክንያት አንድ አይነት መድኃኒትን በተለያየ የንግድ ስም እና ዋጋ በገበያ ላይ ልናገኝ እንችላለን። የዋጋው መለያየትም ከየአምራች ድርጅቶቹ የምርት ወጪ ሁኔታ እና የትርፍ ፍላጎት ጋር የተያያዘ ነው።

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482
http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ